# ተስፋሁን አለምነህ የቀድሞ የመኢ’አድ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ሃላፊ ዛሬ በሰላም ወደ ሃገሩ ገባ

September 9, 2018



በጣም ጎበዝ፣ ታታሪካ አገሩን የሚወድ። ያኔ መኢ’አድና አንድነት እንዲዋሃዱ ትልቅ ስራ ይሰራ የነበረ ወጣት ነው። ከተስፋሁን ጋር በጣም አግባብ ነበረኝ። ሞቶ በሞቶ ምርጫ አሸነፍን ሲሉ ተስፋሁን ተስፋ ቆረጠ። ብዙ ነገር ያማክረኝ ነበር። ግን አንድ ወቅት ለሳምንታት ጠፋብኝ። እንዳይሄድ እንደማከላክለው ስላወቀ አላማከረኝም። ኤርትራ ገባ። ኤርትራ መግባቱን ለኢሳት ሰማሁ። በአንድ በኩል አዘንኩ በሌላ በኩል ወኔው አኮራኝ።

አንዳንድ “አርበኞች” ተመችቷቸው፣ ወፍረው፣ አምሮባቸው ስላየሁ ተስፋሁን በዚህ መልክ ጠቁሮ ከስቶ ሳየው ሁለት አይነት አርበኝነት እንደነበረ ተረዳሁ !!!

ለማንኛው እንኳን ወደ ቤትህ መጣህ ወንድም ተስፋሁን። የጎጃም የጎንደር ገበሬ እርጎ እያጠጣህ በቅርብ የተጎሳቆለው ሰዉነትህ ይመለሳል። ሞተሃል፣ ታስረዋል ተብሎ ስንጨነቅ ነበር።፡ እግዚአብሄር የተመሰገነ ይሁን በሕይወት አቆይቶሃል።

